የደቀ መዝሙርነት መርሐዎች

የትምህርቱ መሰረታዊ ሃሳቦች

የክርስቲያን ሥነ–ምግባሮች

ትምሕርት 3፥
የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት፡- ክፍል 2

የእግዚአብሔር ቃል እና ፀሎት፣ እያንዳንዱ አማኝ ክርስቲያን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዛት ዉስጥ ሲራመድና ሲመላለስ፥ እንዲያጠነክሩት የተሰጡት ሁለቱ እጅግ አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸዉ። የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ማጥናት፣ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ወደ መመሰጥ መምራት አለበት። ከዚህኛዉ በቀደመዉ፥ 'የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ክፍል 1' ትምሕርት ዉስጥ፤ ሮሜ 12:1–2 ያለዉን ጥቅስ እንደ ምሳሌ ወይም መነሻ ሃሳብ ወስደን፡- ማን፥ ምን፥ መቼ እና፥ ለምን፥ የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት፣ በኦብዘርቬሽ ደረጃ ዉስጥ ገብተን በጥልቀት ተንትነን ተመልክተናል። ከመጀመሪያዉ የጥናት ደረጃ ይህንን ያህል መረጃዎችን ከሰበሰብን፣ አሁን ወደሚቀጥሉት፣ ቀሪዎቹ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃዎች ለመሸጋገር ዝግጁ ነን።

የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት በሚል ርዕስ ሥር ከቀረቡት ሁለት ተከታታይ ትምሕርቶች፣ በመጀመሪያዉ ክፍል ዉስጥ፣ ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ባጠቃላይ ምን እንደሆነ በዝርዝር አይተን፤ ከሶስቱ መሠረታዊ የጥናት ደረጃዎች፣ የኦብዘርቬሽን ደረጃን የጥናት አካሄድ በስፋት ተመልክተናል። በዚህኛዉ በክፍል 2 ትምሕርታችን ደግሞ፣ በኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ ዉስጥ፡- የኢንተርፕሪቴሽን እና፣ የአፕሊኬሽን የጥናት ደረጃዎችን ተግባራዊ አጠቃቀም እንቃኛለን።

ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፤ አንድ አማኝ ወይም ክርስቲያን፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ወይም የጥናቱን ክፍል ጽሑፍ፥ ስረ ነገር ወይም መሠረታዊ ትርጓሜ (ኦሪጅናል) ፍች ለማወቅ ሲፈልግ የሚጠቀምበት የጥናት ዘዴ ነዉ። ለጥናቱ ጭብጥ ፍች ለመስጠት ሌሎች ጥቅሶችን እና አገባባቸዉን የሚጠቀምና፤ በተለያዩ ጥያቄዎች አማካይነትም ጽሑፉን በጥንቃቄ የሚመረምር ዘዴ ነዉ። የመጀመሪያዉ ደረጃ፥ የጥቅሱ ጽሑፍ የሚለዉን በማንበብ፥ በመተንተን፥ ማስተዋል ነዉ።

አሁን ሁለተኛዉን ደረጃ አብረን እንመልከት። የእዚህ የኢንተርፕሪቴሽን ደረጃ ዋና አላማ፦እኛን የጥቅሱ ምንባብ ትክክለኛ ትርጉም ምን እንደሆነ እንድናዉቅ ማስቻል ነዉ። ልብ በል፦ እኛ በጥናታችን የምንጥረዉ፣ ደራሲዉ ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ጥቅስ) ሲጽፍ ምን ለማለት፥ ወይም ምን መልእክት ለማስተላለፍ ፈልጎ እንደነበረ ለማወቅ ነዉ። ያንንም ለማድረግ፥ ሦስት እርምጃዎችን መዉሰድ ይጠበቅብናል።

የመጀመሪያዉ እርምጃ፦ በዚህ በኢንተርፕሪቴሽን የጥናት ደረጃ ዉስጥ፥ ማድረግ የሚገባን አንደኛዉ ነገር፤ ስለ ጥቅሱ ወይም ጽሑፉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ነዉ። ምን ብለን? ይህ ንኡስ ክፍል እና ጥቅስ ለምን በዚህ ክፍል ዉስጥ እንዲሆን ተፈለገ? በእዚህስ ጥቅስ ጸሃፊዉ ምን ለማለት ፈልጓል? ብለን እንጠይቃለን።

አሁንም በመጀመሪያዉ ማለት በትምሕርት 1 ዉስጥ፣ አብዘርቬሽን ደረጃን ለመመርመር የተጠቀምነዉን ጥቅስ እንደገና እንዉሰድ፦ “እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።” (ሮሜ 12:1–2)

በዚህ ጥቅስ ዉስጥ ጳዉሎስ የሮምን አማኞች የሚጠይቀዉ፦ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኝን የቅድስና ሕይወት እንዲኖሩ ሲሆን፣ ይኸዉም ሰዉነታቸዉን ሕያዉ መሥዋዕት አድርገዉ እንዲያቀርቡ ነዉ። በአጭሩ፥ የቅድስናን ሕይወት መኖር፤ በእግዚአብሔር ፊት እንደ አምልኮት ድርጊት ይቆጠርልናል። ይህ ጥቅስ በተጨማሪ፦ ይህንን ዓለም ባለመምሰል፤ አእምሮአችንን ለምን ማደስ እንደሚገባን፤ እንዲሁም፥ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለይተን እንዴት እንደምንደርስበት ይነግረናል።

ሁለተኛዉ እርምጃ፦ የበለጠ ለመረዳት፥ በኢንተርፕሪቴሽን ደረጃ ዉስጥ፥ ወደ ሁለተኛዉ እርምጃ እንሸጋገር። በዚህኛዉ እርምጃ፥ ጸሐፊዉ ጳዉሎስ የሚለዉን የበለጠ እንረዳዉ እንደሆነ፣ ከዚህ ጥቅስ ጋራ ተያያዥነት ያላቸዉን የሌሎችን ጥቅሶች ተጨማሪ ሃሳብ፥ ድጋፍ መዉሰድ ነዉ። ለምሳሌ፥ አሁን ከምናጠናዉ ክፍል ጋራ አግባብ ወይም ግንኙነት ያላቸዉ ጥቅሶች፥ ሮሜ 11:13–36 ዉስጥ ይገኛሉ። እዚህ ሥፍራ ላይ ጳዉሎስ፦ የእሥራኤል ልጆች እንዴት ወንጌልን እንዳስወገዱ እና፤ አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት፥ ፀጋዉ ወደ አህዛብ ሁሉ እንዴት እንደተዘረጋና እንደተሰጠ ይገልፃል። በዚሁ ሁኔታ ሮሜ 12፥1 ን ስናነብ፣ ጳዉሎስ መልእክቱን (በእንግሊዝኛዉ መጽሐፍ ቅዱስ

ልብ በል

የእግዚአብሔር ቃል እና ፀሎት፣ እያንዳንዱ አማኝ ክርስቲያን፥ በእግዚአብሔር ፈቃድና ትዕዛዛት ዉስጥ ሲራመድና ሲመላለስ፥ እንዲያጠነክሩት የተሰጡት ሁለቱ እጅግ አስፈላጊ መሣሪያዎች ናቸዉ። የእግዚአብሔርን ቃል ማንበብ፥ የእግዚአብሔርን ቃል ወደ ማጥናት፣ የእግዚአብሔር ቃል ላይ ወደ መመሰጥ መምራት አለበት።

የአፕሊኬሽን ደረጃ፥ ከሁሉም ወሳኝ የሆነና፣ ይዘቱን በብቃት በመገንዘብ አስከተማርንበት ጊዜ የደረስንባቸዉንና የሰበሰብናቸዉን መሠረታዊ መመሪያዎች (መርሆዎች) እንዴት በሕይወታችን መተግበር እንደምንችል የምናይበት ደረጃ ነዉ።

ላይ የቁጥር 1 አጀማመር ከአማርኛዉ ለየት ብሎ፥ እለምናችኋለሁ የሚለዉ ወደ ፊት ይመጣል) “እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእግዚአብሔር ርኅራኄ እለምናችኋለሁ።” ብሎ የጀመረዉ ለምን እንደሆነ እንረዳለን። ይህ ምዕራፍ ሙሉ በሙሉ፦ እንደ አማኝ ክርስቲያን፥ በዚህ ዓለም ዉስጥ፥ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን አካሄድ፥ መልካም ምግባርን በማንፀባረቅ እንዴት መምራት እንደሚገባን ያወሳል።

እስከ አሁን ድረስ፥ ከኢንተርፕሪቴሽን ደረጃ፣ ሁለቱን እርምጃዎች ተመልክተናል። ማለትም፥ የመጀመሪያዉ እርምጃ፦ ጸሐፊዉ ለአንባቢዎቹ ለማስተላለፍና ለማሳየት የፈለገዉ መሠረታዊ ሃሳብ ላይ መድረስ፤ ሁለተኛዉ እርምጃ ደግሞ፦ሌሎች ተጓዳኝ ጥቅሶችን ተጠቅሞ፤ የጥናቱን ጥቅስ ትክክለኛና ጥርት ያለ ትርጓሜ ወይም ፍች ማግኘት ነው።

ሦስተኛዉ እርምጃ፦ አሁን ደግሞ ቀጥለን፥ የኢንተርፕሪቴሽን አጠናን ደረጃ፥ ሦስተኛና የመጨረሻዉ የሆነዉን እርምጃ፦ ማለትም፥ ከጥቅሱ ዉስጥ ተምረን የሚቀሩልንን መርሆች (ፕሪንስፕልስ) ማለትም፥ ልንከተላቸዉና በሕይወታችን ልንተገብር የሚገቡንን ሥነምግባሮች ዝርዝር ማዘጋጀት ነዉ። ሮሜ 12:1–2 ላይ ተመሥርተን በጥልቀት ስንመለከት፥ ከእነዚህ ጥቅሶች የተወሰኑ የክርስትና ሕይወት መሆዎችን እናወጣለን፦

1. ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር ላይ ማተኮር፤ ሁልጊዜም ድርጊቶቻችን ሁሉ እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ ሆኖ መመላለስ፣

2. በዚህ ዓለም ዉስጥ በዙሪያችን ያሉት ሁሉ በሚያደርጓቸዉ ነገሮች አለመሳብና አለመወሰድ፣

3. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሁልጊዜ መፈፀም እንችል ዘንድ፤ አእምሮአችንን ያለማቋረጥ ማደስ።

እንግዲህ አሁን፥ በኢንተርፕሪቴሽን አጠናን ደረጃ ዉስጥ የተመለከትናቸዉን ሦስት እርምጃዎች አጠናቅቀናል። ስለዚህ፥ በኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴ፣ ወደ ሦስተኛዉና የመጨረሻዉ ደረጃ፦ ማለትም ወደ አፕሊኬሽን ደረጃ ጥናት እናመራለን።

ይህ ደረጃ ደግሞ፥ ከሁሉም ወሳኝ የሆነና፣ ይዘቱን በብቃት በመገንዘብ አስከተማርንበት ጊዜ የደረስንባቸዉንና የሰበሰብናቸዉን መሠረታዊ መመሪያዎች እንዴት በሕይወታችን መተግበር እንደምንችል የምናይበት ደረጃ ነዉ። ለምሳሌ፦ በኢንተርፕሪቴሽን ደረጃ ካገኘናቸዉ ሦስት መርሆዎች አንደኛዉ፤ ሙሉ ለሙሉ እግዚአብሔር ላይ ማተኮር፤ ሁልጊዜም ድርጊቶቻችን ሁሉ እርሱን ደስ እንደሚያሰኙ ሆኖ መመላለስ ነዉ። ይህንን መርህ በሕይወታችን ተግባራዊ የምናደርገዉ እንዴት ነዉ? አንደኛ፦ ወደ ሃሳባችን አትኩረን በመመልከት፥ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኙ መሆናቸዉን እርግጠኞች መሆን፤ ሁለተኛ፦ ማንኛቸዉንም ድርጊቶቻችንን በመመርመር፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚከናወኑ መሆናቸዉን ልብ ማለት ይገባናል። ሦስተኛ፦ በማንኛዉም ጊዜና ሁኔታ የምንናገራቸዉን ሁሉ፣ በጥንቃቄ ማስተዋል ይገባናል፤ ምክንያቱም፥ በምላሳችን ላይ ሕይወትም ሞትም አለና። ከእነዚህ ሁሉ ጎን፤ ዕቅዶቻችንና ዉሳኔዎቻችን ሁሉ በእግዚአብሔር ቃል እና በእርሱ ፈቃድ ላይ የተመሠረቱ መሆን ይገባቸዋል።

በጥልቀት እንይ

ሦስቱ የኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃዎች፦ አብዘርቬሽን፥ ኢንተርፕሪቴሽን እና፣ አፕሊኬሽን ናቸዉ።

የኢንተርፕሪቴሽን ደረጃ ዋና አላማ፦ እኛን የጥቅሱ ምንባብ ትክክለኛ ትርጉም ምን እንደሆነ እንድናዉቅ ማስቻል ነዉ። ልብ በል፦ እኛ በጥናታችን የምንጥረዉ፣ ደራሲዉ ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል (ጥቅስ) ሲጽፍ ምን ለማለት፥ ወይም ምን መልእክት ለማስተላለፍ ፈልጎ እንደነበረ ለማወቅ ነዉ።

ማጠቃለያ

- የኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለተኛዉ ደረጃ፣ ኢንተርፕሪቴሽን ይባላል። ይህም ደረጃ በሦስት እርምጃዎች ይከፈላል።

- የመጀመሪያዉ እርምጃ፡- ጸሐፊዉ ለአንባቢዎቹ ለማስተላለፍና ለማሳየት የፈለገዉ መሠረታዊ ሃሳብ ላይ መድረስ ነዉ።

- ሁለተኛዉ እርምጃ፡-አሁን ከምናጠናዉ ክፍል ጋራ አግባብ ወይም ተያያዥነት ያላቸዉን ሌሎችን ጥቅሶች በማፈላለግ፣ ለግንዛቤአችን የሚፈነጥቁትን ብርሃን ማየት ነዉ።

- ሦስተኛዉ እርምጃ ደግሞ፣ አፅንተን በማጥናት ካገኘነዉ ትርጓሜ (ፍች) የሚቀሩልንን መርሆዎች ለይቶ ማዉጣት ነዉ።

- እነዚህን ሦስት እርምጃዎች ካጠናቀቅን በኋላ፣ አፕሊኬሽን ወደ ተባለዉ ሦስተኛዉ የኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃ እንሸጋገራለን። በዚህ ደረጃ ዉስጥ፣ በብዙ ጥናት አግኝተን የለየናቸዉን መርሆዎች ሁሉ በሕይወታችን ላይ ተግባራዊ እናደርጋለን።

እርስዎስ ምን ይላሉ?

- ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን ሞክረህ ታዉቃለህን? በእግዚአብሔር ሕግጋትና ፈቃድ ዉስጥ እንድትመላለስ የረዳህስ እንዴት ነዉ?

- በአከናወንከዉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሠረት፣ እግዚአብሔር እንድትለዉጥ የሚጠይቅህ የትኞቹን የሕይወት ገጽታዎችህን ነዉ?

- ኢንደክቲቭ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን ስትጠቀም፣ ሮሜ 12 ዉስጥ ልታገኝ የምትችለዉ ሌላኛዉ መርህ ምንድን ነዉ?

ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች በ 1954 ዓም ከታተመዉ የድሮዉ (KJV) ትርጉም ሲሆን፣ በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ፈቃድ ተቀድቶ የታተመ ነዉ።

ሌሎች ሁሉም ይዘቶች የ © 2019 ትራንስ ዎርልድ ራዲዮ ካናዳ ነው። ይህንን ግብአት ለመጠቀም ዋጋ እስካልጠየቁ ድረስ እና ስለ ክርስቶስ አለምን መድረስን አላማዎ አድርገዉ እስከሰሩ ድረስ በፈለጉት አይነት መንገድ ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ተጨማሪ የፍቃድ ዝርዝሮችን በ www.discipleshipessentials.org/licensing ይመልከቱ.